# ለዴንቨር ኮሎራዶ ሃቀኛ ኢትዮጵያን ሁሉ ጥሪ አለኝ!

ፍትህ ከሰሜን አሜሪካ

8/25/2013

የንጽሃንን ወጣት ደም በግን አለብኝ ያፈሰሰው አረመኔው **ከፍያለው ዓለሙ** እናንተ ባላችሁበት አገር ተደብቆ ይኖር እንደነበር ዛሬ ገሃድ ወጥቶ ሁላችንም አወቅነው፡፡ እናንተንም እኛንም ለጥቂት አመታት ሸውዶናል፡፡ የሟቾቹ ደም ለፍትህ ሲጮህ ዘመናት ቢያልፍም ቀኑን ጠብቆ በአቶ **ከፍሉ ከተማ** ተግባራዊ ወደመሆን ደረጃ ሊደርስ ችሏል፡፡ ይህ ጉዳይ የአቶ ዓለሙ ጉዳይ ብቻ እንዳልሆነ ግልፅ ነው፡፡ እንዲያውም ጉዳዮ የኢትዮጵያውያን ብቻ አይደለም፡፡ ጉዳዮ አለም አቀፋዊ ሆናል፡፡ በየትኛውም ቦታ በሰው ልጅ ላይ የሚካሄድ ግፍ በማኝኛውም የፍትህ ደጋፊ ሕብረተሰብ ከፍተኛ ተቃውሞ ይገጥመዋል፡፡ አቶ ክፍሉን ዓላማ በመደገፍ በርካታ ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ ሰዎች ወደ ፍርድ ቤት እንደሚሄዱ ሰምተናል፡፡ በነሱ መካከለ ያለው አንድ ኢትዮጵያዊ ግን አቶ ክፍሉ ብቻ መሆኑን ስምቻለሁ፡፡ ምነው ዴንቨር ዜናውን አልሰማችሁም እንዴ እኔ እንካን ከ600 ማይልስ እርቀት ዜናውን ስሰማ ለናንተ ባዳ ሆነባችሁ? እንዴት አንድ ሰው ወደ ፍርድ ቤቱ በመሄድ ድጋፍን ማሳየት ሰነፈ? በዴንቨር ኑአሪ የሆናችሁ ሃቀኛ ኢቲዮጵያውያን ከዚህ በላይ መድረግ አያቅታችሁና 10/07/2013 ከፍርድ ቤቱ እንገናን፡፡

አለመታደል ሆኖ የዚህ አካይስት ሰው ሰለባ የሆኑት ወጣቶችን በካዛንችስ አካባቢ በመኖሬ አውቃቸዋለሁ፡፡ ከመካከላቸው በጣም የቅርቤ የሆነ እብሮ አደግ ወዳጄ አሸናፊ በቀለ የተባለ ወጣት ይገኛል፡፡ ያሸናፊ ደም ለሱ ብቻ ሳይሆን አብረውት ለታረዱት ወጣቶች እንድጮህ ይጎተጉተኛል፡፡ አቶ ክፍሉ ለሁሉም ተቆርቃሪ በመሆን መቆሙን የሰማሁት በታላቅ አክብሮት ሲሆን ለደረሰበት ግፋዊ በትር ልቤ ማዘኑን መደበቅ የለብኝም፡፡ የኒያ ወጣቶች ደም በአቶ ክፍሉ ትግል ፍትህ ያገኛል ብዬ ባምንም ተከራካሪ መሆን የሚገባው እሱ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ሃቀኛ ኢትዮጵያዊያን መሆን አለብን፡፡ በተለይ ዴንቨር ያላችሁት ኢትዮጵያዊያን በፍርዱ እለት ወደፍርድ ቤቱ በመሄድ በግፍ ለተገደሉት ኢትዮጵያውያን መቆም አለባችሁ፡፡

***ይህን ጉዳይ እንዴት ማገዝ ይገባናል?***

- ዴንቨሮች የፍርዱ ቀን ወደፍርድ ቦታው መሄድ አለባችሁ
- በአለም ዙሪያ ያለን ኢትዮጵያውያን ደግሞ የድጋግ ደብድዳቤ ኢሜል ፋክስ በማድረገ አቶ ክፍሉን በሞራል መደገፍ
- የሰበአዊ ሙብት ተከራካሪዎች የድጋፍ ደብዳቤ ወደ አቶ ክፍሉ መላክ ከትቻለም ለጠበቃው ወይም ለፍርድ ቢቱ መላካ
- በፍትህና በዴሞክራሲ የምታምኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ድግፍ ደብዳቤ መፃፍ ትንሹንስ ዋጋ መክፍል ነውና በርቱ

ለማንኛውም በቀጥታውኑ አቶ ክፍሉን በስልክ ቁጥር **720-329-5692** በመደወል ማነጋገር ይቻላል፡፡

ዴንቨሮች በፍርድ ቤቱ ቀጠሮ ቀን 10/07/2013 ከጠዋቱ 8፡00 am Denver down town 901 19th st በመገኘት መተባበር ይገባናል።።

በእለቱ ከአቶ ክፍሉ ጎን ለመቆም እቅድ አለኝ ከቁጥጥሬ ውጭ የሆነ ጉዳይ ካላጋጠመኝ፡፡